# ጊዜው የሚጠይቀው ተቃዋሚነትን ሳይሆን አማራጭ መንግስት መሆንን ነው ።

ተቃዋሚዎች ምርጫው ላይ የሚካፈሉበት ዋናው ምክንያት አብላጫ የህዝብ ድምጽ አግኝተው መንግስት ለመሆን ነው። አንድ ድርጅት ምርጫ እወዳደራለው ብሎ የምርጫ ውድድር ከጀመረ በኋላ እንደተቃዋሚ ሳይሆን እንደአማራጭ መንግስት ነው እራሱን ለመራጩ ህዝብ ማቅረብ ያለበት።

እራሳቸውን እንደአማራጭ መንግስት ማየት ብቻ ሳይሆን ገዢው ፓርቲም እንደ አንድ እጩ ተወዳዳሪ እንዲታይ ማድረግ አለባቸው። ይህ አስተሳሰብ ከነሱ አልፎ ተጽኖው መራጩ ህዝብ ዘንድ በደንብ እስኪሰማ ድረስ። በተገኘው አጋጣሚም ከዚህ በኋላ የሚያደርጉት ማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ ይህ መልክት እንዲሰማ ሆኖ መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

የምርጫ 97 ላይ ተቃዋሚዎች የመራጩን ድምጽ በገፍ ማግኘቱም በኋላ ላይ ውጤቱን ለመጠበቅ ያልቻለብት ምክንያት ቁምነገሩ ይህ ነው። አሸንፌው እንደአሸናፊ መተወን አልቻሉም። አሁንም ይህ አስተሳሰብ ከምርጫው ውጤት በኋላም መቀጠል በሚችልበት ሁኔታ እራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

አሸናፊ መሆናችንን እርግጠኛ ሆነን መንግስት ስንሆን የሚለውን ለማስረጽ ደግሞ በይበልጥም እየገዛ ካለ ፓርቲ ጋር የሚወዳደር ፓርቲ እሱ ሊያደርገው ያቃተውን፣ ማድረግ እንደሚችሉ። ያበላሸውን ማስተካከል እንደምንችል አቅሙም እውቀቱም ዝግጅቱም እንዳለ ማሳየት አንዱ መንገድ ነው። አይደለም እናንተ መንግስት ሆናችሁ ወያኔም ቢቀጠል ወደመጥፎም ይሁን ወደጥሩ የተወሰኑ ነገሮች እንደሚለወጡ ህዝብ ይገምታል። የምርጫ ውድድር ላይ ሆኖ እንደምናደርገው ህዝብ ያውቃል ብሎ ነገር ግን አይሰራም።

እነመለስ ሚዲያውን ነጻ ማድረግ ስለፈሩ አልቻሉም። እናንተ መንግስት ስንሆን ማናቸውም ሚዲያዎች ያለምንም ተጽኖ ነጻ ሆነው እንዲሰሩ እናደርጋለን። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራዲዮን ይጨምራል ይህ አቀራረብ ምን ችግር አለው። አቀራረቡ ተአማኒ እንዲሆን። የአዲስ ነገር ጋዜጠኞች ወደአገራቸው ተመልሰው ይሰራሉ። የሚፈልገው አንድ የስልክ ጥሪ ነው። እነሱም ሌሎችም በነጻ መስራት ስላልቻሉ ከአገር የወጡ ጋዜጠኞች በሙሉ ጉዳዩ ላይ እውቅናን እንዲሰጡ ማድረግ በጅ ያለ ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ የኪነት ሰዎችን ምሁራንን። አገር ቤት ከአሉት ዶክተሮች በላይ ቁጥር ያላቸው ዶክተሮች በውጪ ነው ያሉት። ከሁሉም ጋር ስምምነት ለማድረግ ማን ነው የሚከለክላቸሁ። ስታሸነፉ መንግስት ልትሆኑና አገር ላታስተዳድሩ እኮ ነው።

የሚወዳደራችሁ ሀይል አግላይ ነው። ፖለቲካል መፍትሄ መፈለግ ስላልቻለ ብዙ ድርጅቶችን ሽብርተኛ አስገንጣይ ነፍጠኛ እያለ በጦርነት መፍታቱን ችግሩን ማወሳሰብ መርጧል። ስምምነት ሰርቶ ለቀረበ ሀይል ሊያስገኝ የሚችለው ድጋፍ ያለው ፖለቲካል ጠቀሜታ ቀላል አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብም እናንተም ችግሩ የፖለቲካ መሆኑን ታውቃላችሁ። በቀጣዩ መንግስት መሆን የሚፈልግ ሀይል የተሻለ

የመንግስትነት ባህሪን ተላብሶ ለመቅረብ እዚህ ችግር ላይ መፍትሄ ሰርቶ ነው መቅረብ ያለበት።

እነዚህ ድርጅቶች ሁሉ አገሪቷ ያለችበትን ችግር። ምርጫው የሚደረግበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ያለውን አንገብጋቢ የጊዜ ችግር ከናንተ በላይ ያውቃሉ። ከተሞክሮ ብዙዎቹ በምርጫ ለውጥ ይመጣል ብለውም አያምኑም። እንሞክራለን ከአላችሁ እውቅናን ለመስጠት ችግር አይኖርባቸውም። ዝርዝር ውስብስብ ጌዜ የሚወስድ ስምምነትም አይጠብቁም።

እናንተ ስላላደረጋችሁት፣ ሀሳቡ ከናንተ ስላልመጣ የሚመለከታቸው ሁሉ ህዝብ ድምጹን ለናንተ እንዲሰጥ እውቅናን ከአልሰጡም ፋሮች ናቸው። እስካሉብን ችግሮች የመጨረሻው ፍራቻ ድረስ ብንወስደው ለመታገል ማን ይቀላል የሚለው ጉዳይ ይኖራል። ይህ ግን የናንተ ዋንኛ ስራ ነው። የጊዜ የሰው ሀይል እጥረት ሰበብ አይሆንም። ስሩት ከአላችኋቸው ይህን ሀላፊነት መወሰድ የሚችሉ የድጋፍ ድርጅቶች አሏችሁ። ስራውን ለመስራት በቂ ችሎታ አላቸው።

የአንድነትን ሊቀመንበር ጨምሮ አቶ አበራ የማነአብ፣ ደብተራው ከማናውቃቸው ኮ/ል ተስፉ ሀይሉን የመሳሰሉ የቅንጅት ደጋፊ ስለነበር ብቻ መሳርያ ለቅንጅት አቀበልክ በሚል የፈጠራ ክስ ታስሮ ያለ። ሌሎችም በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ በፖለቲካ ምክንያት የታሰሩ አሉ።

የፖለቲካ እስረኛ ለመኖሩ የወ/ት ብርቱካን ብቻ ከበቂ  በላይ ማረጋገጫ ነው። መድረኩም ሆነ መኢአድ ቢያሸንፍና ስልጣን ቢይዙ እነዚህ የፖለቲካ እስረኞች እንደሚፈቱ እናውቃለን። ቁም ነገሩ ግን ዜጎችን በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት የሚያስር ድርጅት ጋር ምርጫ እየተወዳደርን። በመራጩ ህዝብ ዘንድ ይህ ችግር አሳሳቢነቱ ከፍተኛ ሆኖ እያለ መንግስት ለመሆን የተዘጋጀ ተቃዋሚ ገዢው ፓርቲ ስለሚለው ማሰቡን አቁሞ የፖለቲካ እስረኞች ላይ ምን እንደሚያደርግ ግልጽ የሆነ ፖሊሲ ይዞ መቅረብ አለመቻል ውድድር ውስጥ እንዳለ መዘንጋት ነው።

እኛ መንግስት ስንሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እስረኛ አይኖርም። ታስረው ያሉትንም ህግና ደንብን በተከተል አጣሪ ኮሚሽን አቋቅመን በፖለቲካ እምነታቸው የታሰሩትን በሙሉ እንፈታለን። የአለአግባብ ለተንገላቱበትም አግባብ ያለው ካሳ እንከፍላለን። የህዝብ ድጋፍን የሚያስገኝ፣ በአላንጣን የሚሳንስ አግባብ ያለው አቀራረብ ነው።

በዛሬይቷ ኢትዮጳያ ወያኔ በጥቅም ያልተደለለ ከአልሆነ ባዶ የህዝብ ድጋፍ እንዳለው እናውቃለን። ተቃዋሚዎች ላይ እጃችሁ ከምን የሚለው ጥያቄ በግልም በተሰባሰበ ሁኔታም ብዙም አሳሳቢ ለአይሆን ይችላል። ይህ ማለት ግን አላስፈላጊ መልስ የማያስፈልገው ጥያቄ ነው ማለት አይደለም። ሁሉም ዜጋ ደግሞ ወያኔን አለመፈለጉ እንዳለ ለዚህ ጥያቄ መልስ አይሻም ማለትም አይደለም። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስረአቱን የማይፈልግ ነግር ግን የስረአቱ አካል የሆነ ዜጋም እንዳለም መዘንጋት የለብንም።

ጠሩ፤ ደህንነቱ፤ ፖሊሲ … እናንተ መንግስት ስትሆኑ የሚያገኙት አዲስ ነገር ምንድን ነው። ደሞዝ ጭማሪ አንገብጋቢ ጥያቄያቸው አይመስለንም። ከሆነም ግን እናንተ መንግስት በመሆናችሁ ከሚያገኙት አንዱ ነገር ማድረግ ትችላላችሁ።

በተመሳሳይ ለነጋዴው፤ ለአስተማሪው፤ ለተማሪው፤ ለጤና በአለሞያው ምንድነው የምታስገኙላቸው።

የፓርቲ ፕሮግራም አለ ልንል እንችላለን። በመጀመርያ የፓርቲ ፕሮግራም አሰራሩ ራሱ ለምርጫ እንዲያመች አይደለም። ለሁሉም ዝርዝር የለውም። መራጩ ህዝብ ያን እያነበበ ይመርጣል የምትሉ ከሆነ የምርጫ ዘመቻም ማካሄድ በአልስፈለጋችሁ ነበር። ለመራጩ ህዝብ በወረቀት ላይ ካለ ከተቻለ በአካል ያም ከአልሆነ በቃል መናገር የበልጣል። መናገር ጀምሩ።

እነዚህና እነዚህን የመሳሳሉ ነገሮች ልታደርጓቸው የምትችሉ በፍጹም ከባድም ያልሆኑ ናቸው። በሳምንት አንዴ ጋዜጣዊ መግለጫ እያደረጋችሁ እየከፋፈላችሁ በአማረ መልክ በትንሽ በትንሹ ማውጣት ትችላላችሁ። በተገኘው ህዝብን መድረሻ መንገድ ለህዝብ ለማድረስ መጣር አለባችሁ። ስብሰባ አስተማሪውን ለብቻ፤ ዶክተሩን ለብቻ፤ ተማሪውን ለብቻ፤ ነጋዴውን ለብቻ፤ ታክሲ ነጂውን ለብቻ መጥራት አለባችሁ። መንግስት ልትሆኑ ነው እንደማይቻል ይታወቃል ፖሊሲ ለምንደፍ ከጠሩ ጋር ለመምከርም መጠየቅ አለባችሁ። መከልከሉም ተገናኝቶ የመምከሩን ያህል ነው።

የባለእውቀት የጊዜ እጥረት ካለ ከሚፈለገው በላይ እውቀቱም ፍላጎትም የአላቸው ዜጎች አሉ። እገዛችሁን እንፈልጋለን ብቻ ነው የሚፈልገው። በተረፈ ለመስራት አቅማችን የሚፈቅደውን ሳንሰራ ወይ ችላ ስንል ነው ህዝብ ዘንድ ተአማኒነትከም ለአንባገነኖችም የምንመቻቸው።

Dakotareserch@yahoo.com
Thursday, February 4, 2010